# አምልኮ #1

## ለጥናቱ የመግቢያ ሃሳብ

ሽቱ እንደሚታወቀው ሰዎች ከጥንት ጀምሮ ለተለያዩ ሁኔታዎች በማዋል የሚጠቀሙበት ነገር ሲሆን ከነዚህም መሀል ለነገስታት በስጦታ መልክ በማቅርብ፥ ለቀብር ማዘጋጃነትና እንዲሁም ቀሳውስትንና ነገሥታትን ለመቀባትም ጭምር ይገለገሉበት እንደነበረ ይታወቃል።

ጌታችን በምድር በተመላለሰበት ወቅት ወደ እርሱ የመጡትን ሰዎች ስናስብ አብዛኛዎቹ ከእርሱ የሚፈልጉና ከእርሱ ለመቀበል የመጡ ሰዎች እንጂ ለእርሱ የሚገባውን ለመስጠት ወደ እርሱ ሲመጡ አናይም። ከፊታችን ባሉት ሳምንታት ልናጠናቸው ያሉትን ሶስት ጥናቶች ስንመለከት ግን ለጌታቸው ይገባዋል ብለው ያመኑበትን፥ የከበረ ብለው የያዙትንና እጅግ ውድ የሆነውን ስጦታቸውን ከውስጥ ከመነጨ ፍቅር ጋራ ያበረከቱትን ሴቶች እንመለከታለን።

በማርቆስ 14፥3-9 እና በዮሐንስ 12፥1-9 ውስጥ የተተረኩት አንድ እንደሆኑና በተለያዩ ጊዜያት የሆኑ ነገሮች እንዳልሆኑ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች ያምናሉ። በሁለቱ ታሪኮች ውስጥ የሰፈሩትን ሃሳቦች ስናጤን እውነትም ከዚህ የተለየ ነገር ለማለት ያዳግታል። ሆኖም ይህንን በተመለከተ ብዙ የሚያከራክረን ምክንያት ባይኖርም በማር 14፥3-9 ያለው ክፍል የተካሄደው በቢታንያ ሲሆን በለምፃሙ በስምዖን ቤት በመሆኑና በተጨማሪም ደግሞ ቁ 1 ሁኔታው የተካሄደበት ቀን ፋሲካ ሁለት ቀን ብቻ ሲቀረው መሆኑን ያረጋግጣል። በአንፃሩ ደግሞ ዮሐ 12፥1-9 ስናጠና ግብዣው የተካሄደበት በማርያምና በማርታ ቤት ይመስላል። ሁኔታው የተፈጸመበትን ጊዜ ሲታይ ደግሞ ከፋሲካ ስድስት ቀናት ያህል ቀደም ብሎ መሆኑን ቁ 1 ስለሚነግረን በማርቆስ ከሚገኘው ታሪክ ጋራ ልዩነቱን በማየት ምናልባትም ሁለት በተለያዩ ጊዜያት የተፈጸሙ ሁኔታዎች ሊሆኑ እንደሚችሉም ማሰብ ይቻላል። በዚህም ሆነ በዚያ በማር 14፥3-9 በሚገኘው ክፍል ላይ በመመርኮዝ እግዚአብሄር ሊሰጠን ያለውን እውነት ልባችንን ከፍተን ለመማር እንዘጋጅ።

በኢየሱስ ላይ ሽቶ የፈሰሰባቸውን የተለያዩትን ክፍሎች ስናጠና ብዙ የጋራ የሆኑ ሃሳቦች እንዳሉአቸው እንመለከታለን። ከነዚህም ጥቂቶቹን ለመዘርዘር ያህል፦

- ሽቱ ያፈሰሱት ሁሉም ሴቶች ናቸው።
- ሁሉም ያደረጉት ለየሱስ ነበረ።
- ማናቸውም ሰውን አላስፈቀዱም።
- ሁሉም ያደረጉት ሰዎች በተሰበሰቡበትና በግልጽ ነበረ።
- ሁሉም ነቃፊ ነበረባቸው።
- ኢየሱስ የሁሉንም የፍቅር ስጦታ እንደተቀበለ አረጋግጧል።

# ጥናት አንድ ማርቆስ 14፡3-9 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ይህ ሽቱ ዋጋው እጅግ ውድ ነበረ፣ ያክተቀላቀለ ንጹህ ሽቱ ነው፣ ከሶስት መቶ ዲናር በላይ ሊሸጥ የሚችል ሽቱ ነበረ።
2. አንዳንዶቹ የተቆጡበት ምክንያት በኢየሱስ ላይ ፈሶ ከሚባክን ብዙ ድሆችን ሊጠቅም ይችላል ብለው ስላመኑ ነው። የኢየሱስ መልስ አታስቸግሯት፣ መልካም ነገር አድርጋለች አላቸው።
3. ተሸጦ ለድሆች መስጠትን የተቃወመው ድሆች አያስፈልጋቸውም ብሎ ሳይሆን እውነት ለድሆች ካሰባችሁ ድሆች ሁልጊዜ ከእናንተ ጋራ ናቸው በሰው ገንዘብ ሳይሆን ራሳችሁ ልትረዷቸው ዕድሉ አላችሁ ነው የሚላቸው።
4. ዮሐ 12፡1-8ትን ስናነብ ዮሐንስ ከተቃዋሚዎቹ ንግግር በስተኊላ የነበረውን ስውር ምክንያት ሲገልጥ ይሁዳ ከከረጢቱ ውስጥ መስረቅ ስለለመደ እንጂ ለድሆች ተቆርቁሮ እንዳልሆነ ገልጦ ይነግረናል።
5. በቁ4-5 ላይ እንደምንመለከተው ሰዎቹ ለኢየሱስ የሚያደርጉት አንድም ነገር ሳይኖር ነገር ግን ያላትን እጅግ ውድ ነገር ከፍቅር የተነሳ የሰጠችውን አንድ ሴት ይነቅፉ ነበረ። ከዚህች ሴት ድርጊትና ከኢየሱስ ንግግር እነዚህ ሰዎች ኢየሱስን ማፍቀርና ውዱን ለእርሱ መስጠት ምን እንደሆነ መማር ይችሉ ነበረ። ከሁኔታው ከመማር ይልቅ ግን አድራጊዋን መንቀፍ መረጡ ማለት ነው።
6. በዚህ ክፍል ‹‹…እኔ ግን ሁልጊዜ ከእናንተ ጋራ አልኖርም›› ማለቱ በሥጋ አግኝታችሁኝ ሽቶ ሰብራችሁ ሰውነቴን ልትቀቡት አትችሉም ማለቱ እንጂ በመንፈሱ ከልጆቹ ጋራ እንደማይሆን መናገሩ አይደለም።
7. ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ከፍቅር የተነሳ የምናደርገው ማናቸውም ነገር በስውር እንኳን ብናደርገው በላይ ያለው ጌታ ተመልክቶ መታሰቢያ እንደሚጻፍልንና ድርጊታችን ከንቱ ሆኖ እንደማይቀር ያስተምረናል።
8. እያንዳንዱ የየራሱን ሃሳብ በመናገር ውይይት ይደረግ።

# ጥናት ሁለት ሉቃስ 7:36-43 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ከሁለት ያላነሱ ሰዎች የተነበበውን እንዲናገሩ እድል ይሰጥ፡፡
2. ይህችን ሴት ሃጥያተኛ ያሰኛት ምናልባትም በሴተኛ አዳሪነት የምትተዳደርና ያንንም ሁኔታ የከተማው ሰው ሁሉ የሚያውቅ ሳይሆን አይቀርም፡፡ በተለይ የተሰበሰቡትና ጋባዡም ጭምር አይሁዳዊያን ስለሆኑ ይህ በውግራት የሚያስቀጣ ነገር ነው፡፡
3. ፈሪሳዊው ጋባዥ ይህችን ሴት ሃጥያተኛና ከኢየሱስ አጠገብ መድረስ የማይኖርባት አድርጎ ነው ሲገልጣት የሚታየው፣ ኢየሱስ ግን የመጣው ለሐጥያተኞች መሆኑን ስለሚያውቅ መልካም ነኝ ብለው ተኮፍሰው ከተቀመጡት ይልቅ ይህች ሴት ምህረቱን እንደሚያፈስላት ነው የሚነግረው፡፡ እኛም ምንም ያህል ሃጥያታችን ለሰዎች የበዛ ቢሆን፣ በኢየሱስ እግር ስር እስከመጣን ድረስ ምህረት መቀበላችን የማይቀር ነው፡፡
4. እነዚህ ይህች ሴት ያደረገቻቸው ነገሮች ዘወትር የተለመዱ ዓይነት ድርጊቶች ሳይሆኑ የተለዩ ነገሮች ናቸው፤ ይህም የሚያሳየን ለኢየሱስ ያላትን አክብሮትና አለኝ የምትለዋን ሽቶዋን ብቻ ሳይሆን ክብሯ የሆነውን ጸጉሯን እንኳን ሳትቆጥብ ለማበሻ መጠቀሟ ልቧ የት እንዳለ ያሳየናል፡፡
5. ከዚህ ፈሪሳዊ አነጋገር የምንረዳው አንድ እውነት ቢኖር ኢየሱስ ክርስቶስ ነብይ መሆኑን እንኳን አምኖ ያልተቀበለ ሰው እንደሆነ ነው፡፡
6. በልቡ ያሰበውን ኢየሱስ ማወቁ አምላካዊ ባህር እንደነበረው ያረጋግጥልናል፡፡
7. ኢየሱስ ለዚህ ግብዣ ተገቢ እንዳልሆነች ቢያውቅም የእርሱ ልብ በምግቡና በልብስ በውጫዊ ነገር ላይ ሳይሆን የውስጥ ነገር ላይ ስለነበረ የተማረከውና የተቀበላት ለዚህ ነው፡፡
8. ከዚህ መማር የምንችለው በኢየሱስ ደስ ልንሰኝና ደስ ልናሰኘው ስንወስን ተቃውሞ እንደሚኖርና የሚያስከፍለውን መስዋዕትነት ሁሉ ለመክፈል ዝግጁ ልንሆን እንደሚገባን ነው፡፡ ብዛታቸውም ሆነ የእምነት መልክ መያዛቸው ያላስፈራት ምክንያት ልቧ ከኢየሱስ በስተቀር ሌላ ላለማየት ስለወሰነ ነው፡፡
9. እያንዳንዱ የተማረውን ለቡድኑ ያካፍል፡፡

# <u>ጥናት ሶስት ሉቃስ 7፡44-50 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. ልምምዳቸውን ለወገኖች ማካፈል ለሚፈልጉ ሰዎች ጊዜ ይሰጥ።
2. ፈሪሳዊው ለእግሩ ውሃ ማቅረብ ሲገባው አላቀረበም፣ እርሱ ጉንጩን እንኳን አልሳመውም፣ እርሱ ራሱን ዘይት አልቀባውም፤ በሌላ በኩል ደግሞ ሴቲቱ እግሩን በእንባዋ አራሰች፣ በጠጉርዋ አበሰች፣ እግሩን ሳመች፣ አግሩን ሽቶ ቀባች፣
3. በእኔ ግምት ምናልባት ይህ ሰው ኢየሱስን እንደማናቸውም ሰው ስላየውና የነብይነት ሥፍራ እንኳን ስላልሰጠው ይሆናል።
4. ፈሪሳዊው የተባለውን ነገር ሁሉ ያድርግ እንጂ ኢየሱስ ልብ ላይ እንጂ ድርጊት ላይ የሚያተኩር ባለመሆኑ ነው። እኛም ስለአምልኮና አገልግሎት ልንማር የምንችለው ነገር ለኢየሱስ የሚገደው ሩጫና ሽር ጉድ ማለታችን ጉዳይ ሳይሆን ከእርሱ ጋራ የምናጠፋው የጊዜ ዓይነት እንደሆነ ነው።
5. ከዚህ አባባል ልንረዳ የምንችለው ነገር እኛ ሁላችን እጅግ ብዙ ይቅር የተባልን ሃጥያተኞች እንደመሆናችን በዚሁ መጠን ፍቅራችን ለኢየሱስ ብዙ ሊሆን እንደሚገባው ነው።
6. ኢየሱስ ይህንን ሲል ሰውየው ጥቂት ተደግጎልኛል ብሎ የማሰቡን ጉዳይ እንጂ ሴትየዋ ከፈሪሳዊው የበለጠ ሃጥያተኛ ነች ማለቱ አይደለም፤ ምክንያቱም እርሷ በአካል ዝሙት ታድርግ እንጂ ይህ ሰው በልቡ ሰው በማያውቀው እግዚአብሔር ግን በሚያውቀው መንገድ ሃጥያትን ግልጽ ነው።
7. ከኢየሱስ የተቀበለቻቸው ሶስት ነገሮች አንደኛው የሐጥያት ሥርየት(ሃጥያትሽ ተሰርዮልሻል) ሲሆን፣ ሁለተኛው ደህንነት (እምነትሽ አድኖሻል) እና ሌላው ደግሞ ሰላም(በሰላም ሂጂ) ናቸው።
8. በዚህ ጥናት እንደሚታየው እግዚአብሄርን በብዙ የሚወድ ከእርሱ ጋራ በቅርቡ ሆኖ ጊዜ ማጥፋት የሚወድና የከበረ የሚለውን ነገር እንኳን ለእርሱ ሲል ሊጥል ፈቃደኛ የሆነ ሰው ነው እላለሁ። ተከታይ ጥያቄዎች መልሳቸው እንደሰው ሊለያይ ይችላል።
9. እያንዳንዱ የተማረውን ያካፍል።